I. የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ

I. አጠቃላይ መግለጫ

ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስትር

የመሥሪያ ቤቱ ስም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ጠቅላላ ሀኪም III	ህክምና
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት	በ **pBl!K** ሰርቪስ **Â sW hBT L¥T** ሚኒስቴር/ቢሮ ብቻ የሚሞላ	
Ä!RTmNT `§ð	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
	XVI	
መሥሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
bydr©W Æl# -@Â tÌ¥T		

II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ ውጤቶችና ተግባራት

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡

- የህክምና አገልግሎት በመስጠት፣ በሽታን በመከላከል Â -@Â b¥bLiG ፣ መለስተኛ ቀዶ ሕክምና በማድረግ፣ ጥናት ምርምር በማካሄድና ስልጠና በመስጠት፣ የህብረተሰቡን ጤና እንዲጠበቅ ማድረግ ነው።

2.2. የሥራ መደቡ ውጤቶችና ተግባራት

W-@T 1” wd tÌÑ y¸m-# HÑ¥NN ¥kM።

- **የህመምተኞቹን ቅድመ ልይታና መረጣ** (Triaging) **ይሰራል።**
- **አዋቂዎችንም ሆነ ህፃናትን (የውስጥ ደዌን፣ የማዋለጃና ፅንስ ክፍልን፣ የህፃናት ክፍልን እና የቀዶ ሕክምና ክፍሎችን በሚያካትት መልኩ) በድንገተኛና በተመላላሽ ክፍል እና በተኝቶ ህክምና ተቀብሎ የህክምና ታሪክ ቃለመጠይቅና የአካል ምርመራ ያደርጋል፣ የላቦራቶሪ ምርመራዎችን ያዛል።**
- **በምርመራ ውጤቱ ላይ በመመስረት አስፈላጊውን ህክምና ይሰጣል።**
- **በመሳሪያ የታገዙ የማዋለድ አገልግሎት ይሰጣል።**
- ማናቸውንም የበሽተኛውን ግኝትና መረጃዎችን በካርድ ላይ ያሰፍራል።
- **ድንገተኛና መለስተኛ የቀዶ ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ሕሙማን ይለያል።**
- **ስለ ህመምተኛው የህመም ደረጃ እና ከቀዶ ህክምናው ጋር ተከትለው ሊመጡ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ለታካሚው ወይም ለቅርብ ተጠሪው ያስረዳል።**
- **ለመለስተኛና ለድንገተኛ ቀዶ ህክምና ታማሚዎች ቅድመ- ቀዶ ህክምና የምርመራና የህክምና ትዕዛዛትን ይሰጣል፤ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፤ ለቀዶ ሕክምናውም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ሕክምናውን ይሠጣል።**
- **ድህረ-ቀዶ ህክምና ለሕመምተኞችም አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣ የምርመራና የህክምና ትዕዛዛትን ይሰጣል፤ አተገባበራቸውንም ይከታተላል።**
- **የህመምተኛውን የህመም ታሪክ፤ የምርመራ ውጤት እንዲሁም የቀዶ ህክምናውን ግኝት በካርድ ላይ ይመዘግባል።**
- **ሕሙማኑ ሲያገግሙ የጤና ሁኔታቸውን ገምግሞና መዝግቦ ያሰናብታል፤ እንደአስፈላጊነቱ ለክትትሉም ቀጠሮ ይሰጣል።**
- **ከአቅም በላይ የሆኑት የህመም አይነቶችን ለሚመለከለተው ስፔሻሊስት በማማከር አስፈላጊውን ህክምና ይሰጣል እንድአስፈላጊነቱ ወደ ስፔሻሊስቱ ያስተላልፋል።**
- **አገልግሎቱ ከተቋሙ አቅም በላይ የሆኑትን ለይቶ አገልግሎት ወደሚያገኝበት ተቋም ያስተላልፋል።**
- **ተኝተው ለሚታከሙ ህሙማን የጤና ሁኔታ በየአለቁ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ማስተካከያዎች እንዲደረጉ ያደርጋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይቆጣጠራል። ህክምና ሲጨርሱ እንዲወጡ ያደርጋል።**
- **በህክምና ተቋም ውስጥ ህሙማን ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ በምርመራ ያረጋግጣል፣ የሞት ሰርተፊኬትም ይሰጣል።**